*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን*

# ወለደነ ዳግመ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ
# ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ወለደን

*(ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ)*



ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ የሆነው ቅዱስ ጥምቀት የመዳናችን ቁልፍ ጉዳይ ሲሆን የዚህ ቅዱስ ጥምቀት መሥራች የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት ጥር ፲፩ ቀን በቤተ ክርስቲያናችን ከዋዜማው ጀምሮ በደመቀ ሁኔታ ይከበራል፡፡ ይህም የጥምቀት በዓል የመገለጥ በዓል (ኤጲፋንያ) (አስተርእዮ) በመባል ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም የሥግው ቃል የባሕርይ አምላክነት የታወቀበት፣ የሥላሴ አንድነት ሦስትነት የተገለጠበት፣ እኛም ፭ሺ ፭፻ ዘመን አጥተነው የነበረው ነጻነት፤ ማንነት፤ ሰላም፤ ፍቅር፤ ልጅነት የታወጀበት፣ የዕዳ ደብዳቤያችን የተሰረዘበት ታላቅ የድልና የነጻነት ቀን ነው፡፡

## መሠረተ ነገር

ጥንተ ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ይህን ዐለም ሳይፈጥር እሱ ባወቀ በአንድነት በሦስትነት ሲሠለስ ሲቀደስ ይኖር ነበር ‹‹እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ስብሐቲሁ ዘተጸርአ አላ ምሉዕ ወፍጹም ውእቱ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ›› እንዲል፡፡ ይህም ምሥጋናው ጌትነቱ በባሕርዩ እንደቀረ አውቆ ጌትነቱን የሚያመሰግኑና የሚያሥመሰግኑ ግዙፋን ፍጥረታትን ልፍጠር ብሎ አሰበ፤ አስቦም አልቀረ ከእሑድ እስከ ዐርብ ባሉ ፮ ዕለታት የፍጡር አእምሮ አስቦና ተመራምሮ ቆጥሮ ሊደርስባቸው የማይችል

ከአእምሮ በላይ የሆኑ የሚታዩና የማይታዩ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ እጅግ የብዙ ብዙ የሆኑ ልዩ ልዩ ፍጥረታትን ፈጠረ። ከእሊኽም ፍጥረታት መካከል አእምሮ ለብዎ ግዕዛን የተሰጣቸው፣ ስሙን ቀድሰው ክብሩን ወርሰው ሊኖሩ የተፈጠሩ የሰው ልጅና ቅዱሳን መላእክት ናቸው። "ወበእንተዝ ፈጠሮ ለእጓለ እመሕያው ከመ ይትለአኮ በአምሳለ መላእክት" እንዲል። የቀረውን ፍጥረት ግን ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ፈጥሮታል። ይህም ማለት ሰው እሊህን አይቶ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ሊያደንቅበትና ሊያመሰግንበት እሊህን ተመግቦ ሊኖር ተፈጥሯል።

ልዑል እግዚአብሔርም ከፈጠራቸው ፍጥረታት ለይቶ የሰውን ልጅ በሥነ ተፈጥሮ አክብሮታል። ይኸውም ሊታወቅ ከእሑድ እስከ ዐርብ ያሉ ፍጥረታትን ሁሉ በሐልዮ በነቢብ (ለይኩን ባለው ቃሉ) ሲፈጥር ሰንብቶ አዳምን ሲፈጥር ግን ለአክብሮተ አዳም ጭቃ ይዞ ታየ ይለዋልና "ነሥአ መሬተ ወገብሮ ለእጓለ እመ ሕያው" እንዲል።

እንዲህም አድርጎ ነባቢት ለባዊት ሕያዊት ነፍስን አዋሕዶ ሁሉን ግዛ ንዳ ብሎ በሁሉ ላይ አሠለጠነው ‹‹ ወረሰዮ ርዑሰ ወሥሉጠ ላዕለ ኵሉ›› እንዲል።

ከዚህ በኋላ አዳም በተፈጠረ በ፵ ሔዋን በተፈጠረች በ፹ ቀን በልጅነት አክብሮ ብርሃን አልብሶ፣ ብርሃን አጎናጽፎ፣ ገነት አግብቶ፣ በሁሉ ላይ አሠልጥኖ፤ ነገር ግን የጌታን ፈጣሪነት እና የእነርሱን ፍጡርነት የሚያውቅበት ሕግ ሊኾነው ዕፀ በለስን እንዳይበላ ከለከለው።

እሱም ፯ ዓመት ሕጉን ጠብቆ ሥርዐቱን አክብሮ ኖረ፤ ኋላ ግን የሰይጣንን ምክር ሰምቶ ለፍላጎቱ ተገዝቶ ያልተሰጠውን አምላክነት ሽቶ፤ አትብላ ያለውን ዕፀ በለስ በላ። ከትዕዛዙ ወጣ፤ ሕጉን አፈረሰ፤ ከፈጣሪው ጋራ ተጣላ፤ ከገነት ተባረረ፤ ልጅነቱን አጣ፤ ብርሃኑ ተገፈፈ፤ ከክብሩም ተዋረደ።

በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ፣ በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም ተፈርዶበት ወደ ምድረ ፋይድ ወረደ። ከዚህ በኋላ አዳምም በፈታሒነቱ አንጻር መሐሪነቱን ተመራምሮ ብበድለው የፈረደብኝ ይቅር በለኝ ብለውስ ይቅር ይለኝ የለምን ብሎ ንስሓ ገብቶ መሥዋዕት ሠውቶ ቢለምነው ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ሰው ኹኜ ተሰቅዬ ሙቼ ተነሥቼ አድንኃለሁ የሚል አምላካዊ የማዳን ቃል ሰጥቶት ነበርና ቀን ቢደርስ አምባ ይፈርስ እንዲሉ የቀጠረው ፭ሺህ ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከንጽሕተ ንጹሐን ከቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ተወለደ። ሰው ሆነ፤ ሥጋ ለበሰ፤ ሰውም ሆኖ ሕገ ጠባይዓዊ ሕገ መጽሐፋዊ ሲፈጽም አደገ።

ሕገ ጠባይዓዊ መፀነስ፣ መወለድ፣ በየጥቂቱ ማደግ፣ መብላት፣ መጠጣት፣ መራብ መጠማት፣ መተኛት መነሣት ወዘተ.. ሕገ ጠባይዓዊ ይባላል። ሕገ ጠባይዓዊ ማለት የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ብቻ የግድ ሊፈጽማቸው የሚገባው የሰውነት ሕግ ማለት ነው። ጌታም ከብቻዋ ከኃጢአት በቀር የሰውነትን ሥራ ሁሉ ሠርቷልና፤ ‹‹ወኵሎ ሕገ ሰብእ ፈጸመ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ›› እንዲል። ይኸውም ጌታ እሱ ባወቀ ሥርዐተ ጽንስን ሳያፋልስ የዕለት ጽንስ ሆኖ በማኅፀነ ማርያም አድሯል። "ነጽርኬ ኅበ ሠዐሌ ሕፃናት ዘበጥንተ ሙላዱ ወጠነ ፍኖተ ነኪረ አሜሃኬ ተሥዕለ በጥንተ አካል እንዘ ይትወሐድ ቃል ምስለ ሥጋ" እንዲል። ማኅፀኗን ዓለም አድርጎም ፱ ወር ከ፭ ቀን በማኅፀኗ ተቀምጧል። ግዕዘ ሕፃናትንም ሳያፋልስ ሕፃን እንደመሆኑ ሕፃናት የሚሠሩትን ሁሉ ሠርቷል። እንደ ሕፃናትም ሲያለቅስ ተሰምቷል። "ወከመ ሕፃናት በከየ እንዘ ይስእል መጥባተ እሙ ሲሳየ" እንዲል። እንዲህም ሁኖ አምላክ ነኝና ዕለቱን ልደግ ሳይል በየጥቂት በየጥቂቱ አደገ። "በበሕቅ ልህቀ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ" እንዲል። ትምህርት ቤት ገብቶ ፊደለ ዕብራውያን አጠና። እንዲሁም ልብስ መስፋት፣ ቀለም ማግባት ተማረ። ጭቃውን በአዕዋፍ ቅርፅ እየሣለ እፍ ሲልባቸው በደመነፍስ ሕያዋን እየሆኑ

ይበሩ ነበር፡፡ እናቱ እመቤታችን ድንግል ማርያም ያዘዘችውንም ሁሉ በትሕትና ይሠራ ነበር፡፡ ውኃ በወንፊት ቀድቶ፣ እንጨት በደመና ጭኖ በማምጣት እናቱንና የእናቱን ዘመዶች ያገለግል ነበር፡፡ በተአምረ ኢየሱስ እንደተጻፈ “እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ ወለይእቲ እሙ” እንዲል ሕግ ጠባይዓዊ እስከዚህ ነው፡፡

ሕግ መጽሐፋዊ እንደ ኦሪቱ ሥርዓት በ፳ ቀን ቤተ ግዝረት በ፵ ቀን እጉለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዞ ቤተ መቅደስ መግባት፣ ከዓመት ፫ ጊዜ ለገቢረ በአል ኢየሩሳሌም መውጣት ነው፡፡ “እግዚአ ለኦሪት ገብረ በሕገ ኦሪት” ኦሪትን የሠራ የኦሪት ጌታ እሱ ሕገ ኦሪትን ሲፈጽም አደገ፤ “ፈጺሞ ሕገ በዮርዳኖስ ተጠምቀ” እንዲል፡፡ እንዲህ አድርጎ ፴ ዓመት ሲሞላው ‹‹ሖረ ኢየሱስ እምገሊላ ውስተ ዮርዳኖስ ከመ ይጠመቅ እም ኀበ ዮሐንስ›› ያን ጊዜ የትሕትና ባለቤት መምህረ ትሕትና ክርስቶስ በትሕትና ከዮሐንስ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ተነሥቶ ዮሐንስ ወደሚያጠምቅበት ወደ ዮርዳኖስ ሄደ፡፡ ንጹሕ ድንግል መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ሕዝብ ሰብስቦ ጎባኤ ሠርቶ ያስተምር እንዲሁም የንስሓ ጥምቀት ያጠምቅ ነበርና፡፡

ይህም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ የተመረጠ በማኅፀን ሆኖ ለጌታ እንዲሁም ለእናቱ ለእመቤታችን የሰገደ፣ ገና በሕፃንነቱ በሊቀ ካህናቱ በአባቱ በዘካርያስ እጅ ቅብዐ ክህነት ተቀብቶ የብሉይ ኪዳንን ሀብተ ክህነትን ገንዘብ አድርጎ በበረኃ ያደገ፤ የጣመ የላመ ሳይበላ የሞቀ ሳይለብስ በምናኔና በቅድስና የኖረ ንጹሕ ድንግል ካህን ወሰማዕት ነው፡፡ መጻሕፍትም እንዲህ ሲሉ ይመሰክሩለታል፡፡ (ኢሳ 40፥3) ቃለ ዐዋዲ .... በምድረበዳ የሚጮህ ያዋጅ ነጋሪ ቃል....ሚልክ (3፥1) እፌኑ መልአክየ...... መልክተኛየን በፊትህ እልካለሁ፡፡ ጌታም በማቴ 11፥11 ኢተንሥአ እም ትውልደ አንስት ዘየዐቢ እም ዮሐንስ መጥምቅ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥአልተነሣም በማት ተናግሮለታል፡፡

ወደ ጥንተ ነገራችን እንመለስና ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ለመጠመቅ ወደእርሱ ሲመጣ ባየው ጊዜ ዮሐንስም ስለ እርሱ እንዲህ ሲል መሰከረ፡፡ ከእኔ በኃላ የሚመጣው እርሱ ከእኔ አስቀድሞ የነበረ የእግሩን ጫማ ስንኳን ልፈታ የማይገባኝ ከእኔ ይልቅ የከበረ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነው፡፡ እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃችኋል በማለት መሰከረ፡፡ (ማቴ ፫፥፲፭ ዮሐ፩፥፲፭-፴፬) ጌታም ያንጊዜ ደርሶ ‹‹አጥምቀኒ በማይ ከመ ይትቀደስ ማይ በማዕተበ ሰማይ›› ውሃው ይቀደስ ይከብር ዘንድ በውሃ አጥምቀኝ (ድኝ) አለው፡፡ ዮሐንስም ‹‹አንስ እፈቅድ እምኀቤከ እጠመቅ ወአንተኑ ትመጽእ ኀቤየ›› ጌታዬ፣ ባሪያ ወደጌታው ይሄዳል እንጂ ጌታ ወደባሪያው ይሄዳልን? እንደዚሁስ እኔ ወደአንተ መጥቼ ልጠመቅ ይገባኝ ነበር እንጂ አንተ ወደ እኔ መጥተህ ልትጠመቅ ይገባሃልን ‹‹ዕፎ እክል አጥምቆተከ›› እኔ አንተን ማጥመቅ እንደምን ይቻለኛል፡፡

ጌታም መልሶ ‹‹ኅድግ ምዕረስ›› እንዲህ ማለትህን ተው፤ ‹‹ኢይትቄደስ ማይ ለእመ ኢተጠመቁ አነ›› እኔ ካልተጠመቅሁ ውሃው አይከብርም አይቀደስም፤ ‹‹ይደልወነ ከመ ንፈጽም ኵሎ ጽድቀ›› ትንቢተ ነቢያትን ልንፈጽም ይገባናል አለው፡፡ ከዚህም ባሻገር አንተ ጌታውን ያጠመቀ መጥምቀ መለኮት እየተባልክ ክብርህ ልዕልናህ ሲነገር ይኖራል፤ እኔም በባሪያው እጅ ተጠመቀ ተብዬ ትሕትናዬ ሲነገር ይኖራል አለው፡፡ ዮሐንስም መልሶ እሺ ማጥመቁንስ ላጥምቅህ ነገር ግን ‹‹ባዕደ ሶበ አጠምቅ በስምከ አጠምቅ ወበስመ መኑ አጠምቅ ኪያከ›› ሌላውን ሳጠምቅ ባንተ ስም አጠምቃለሁ አንተን ግን ምን ብየ በማን ስም ላጥምቅህ አለው፡፡ ጌታም ‹‹ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየዐትት ኃጢአተ ዓለም ወልዱ ለቡሩክ ከሣቴ ብርሃን ተሣሀለነ›› የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ የአብ የባሕርይ ልጅ ሆይ ይቅር በለን እያልክ አጥምቀኝ አለው፡፡ ከዚህ በኂላ ተያይዘው ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወረዱ፡፡ ያን ጊዜ የዮርዳስ ወንዝ ተጨነቀ፤ ተሸበረ፡፡ ይህንም ሊቁ

እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፤ ወተሐውከ ማየ ዮርዳኖስ እምግርማ መለኮት›› ከመለኮቱ ግርማ የተነሣ የዮርዳኖስ ወንዝ ታወከ፤ ተሸበረ:: ‹‹ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ ማይ ኀበ የሐውር ጸበቦ›› ዮርዳኖስ ዙሪያውን በእሳት ታጠረ፤ ውሃውም ወደየት እንደሚሄድ ቸግሮት ተጨነቀ ሲል ይገልጸዋል:: ጌታም ባለበት እንዲጸና አድርጎ በመለኮታዊ ሥልጣኑ አጽንቶ፣ ‹‹ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መሬታዊ›› እንዲል ሰማያዊ ጌታ በምድራዊ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ:: ‹‹ተርኅወ ሰማይ ወበጥምቀቱ ተዐውቀ መለኮቱ›› ሰማይ ተከፈተ፤ በጥምቀቱ መለኮቱ ታወቀ ተከፈተም ሲል በሰማይ መከፈት መዘጋት ኑሮበት አይደለም ያልታወቀ ምሥጢር ታወቀ ያልተገለፀ ምሥጢር ተገለፀ ሲል ነው እንጅ:: ይኸውም አብ በደመና ሆኖ የምወደው የምወልደው ልጄ ይህ ነው ሲል የወልድ የባሕርይ አምላክነት ተገለጸ፤ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲያርፍ አንድነት ሦስትነት ታወቀ ተረዳ፡ የመገለጥ በዓል የሚባለውም ለዚህ ነው:: ‹‹ወበጥምቀቱ ከሠተ ለነ ብርሃነ›› በመጠመቁም ብርሃንን ገለጸልን ይላል:: ብርሃንም ያለው ልጅነትን ነው:: መጠመቁም ለእርሱ እጠቀምበታለሁ ብሎ ጥቅም ሽቶ የተጠመቀ አይደለም፤ እሱ እከብር አይል በባሕርዩ ክቡር፤ እጸድቅ አይል በባሕርዩ ጻድቅ ነውና::

ጌታ የተጠመቀው የባሕርይ ልጅነቱን ለማስመስከርና አንድነቱን ሦስትነቱን ለመገለጽ፣ እንዲሁም በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የእኛን ጥምቀት ለመቀደስ ‹‹አኮ ፈቂዶ ለተጠምቆ አላ ከመ የሀበነ ሱታፌ ንጽሕ ›› ጥምቀትን ሽቶ ያደረገው አይደለም፤ በንጽሕ አንድ መሆንን ይሰጠን ዘንድ ነው እንጂ:: እርሱ ግን ከእኛ ከሰዎች ዘንድ የሚሻው ምንም ነገር የለም:: (ሃይማኖተ አበው ዘሳዊሮስ ምዕራፍ 87) በሌላ መንገድ ሥርዐተ ጥምቀትን ለመመሥረት አብነት ለመሆን ለጥምቀት ኃይልን ለመስጠት ነው:: እንዲሁም ለቀድሶተ ማያት ውሃዎችን ለመባረክ ዮርዳኖስን ብርሀት ማኅፀን ለማድረግ፤ የዕዳ ደብዳቢያችን ለመደምሰስ ነው:: ከመ ይስዐር መርገማ ለሔዋ ዲበ ዕፀ ተሰቅለ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ እንዲል::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ውሃ መጠመቁም ትንቢቱና ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩን ጌታችን መደኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለምክንያት የሠራው አንድም ሥራ የለም:: ጌታችን መደኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሠራው እያንዳንዱ ሥራ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት ሃይማኖታዊ አስተምህሮና መለኮታዊ የማዳን አላማ አለው:: ከዚህም አንፃር ጌታችን መደኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሠራቸውንም የማዳን ሥራዎች ሁሉ አስቀድሞ ለአባቶቻችን ለቅዱሳን ነቢያት ገልጾላቸዋል:: በመንፈስ ትንቢት ተቃኝተው ትንቢት እንዲናገሩም አድርጓቸዋል:: ‹‹ርእየ ኢሳይያስ ነቢይ በመንፈስ ትንቢት ምሥጢሮ ለአማኑኤል›› እንዲል:: ብርሃነ ዐለም ቅዱስ ጳውሎስም ይህን አስመልክቶ ለእብራውያን በጻፈው መልእክቱ (በምዕራፍ ፩፤፩) ‹‹በብዙኅ ነገር ወበብዙኅ መክፈልት አዕድአ እግዚአብሔር ለአበዊነ በነቢያቲሁ እምትካት›› ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን ለነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዐለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን ለእኛ ተናገረ ብሎ እንዳስተማረን እንዲሁም የቤተክርስቲያናችን ታላቅ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ‹‹አቅዲሙ ነገረ በትንቢት›› ብሎ እንዳስተማረን ጌታችን መደኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ከሆነበት፤ የማዳንን ሥራዎች ከሠራባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የነቢያትን ትንቢት መፈጸም ነበር:: ‹‹ከመ ይፈጽም ትንቢተ በዮርዳኖስ ተጠምቀ›› በዮርዳኖስ ከተጠመቀበትም ምክንያት አንዱ ለነቢያት የገለጸውን ትንቢትና ምሳሌ ለመፈጸም ነው::

ትንቢት፡- እግዚአብሔር በነቢዩ በዳዊት ላይ አድሮ ‹‹ባሕርኒ ርእየት ወጕየት ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅሬሁ›› ባሕር አየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ ብሎ አናግሯል:: (መዝ ፻፲፫(፬)፤፫) ዳግመኛም ‹‹ርእዩከ ማያት እግዚኦ ርእዩከ ማያት ወፈርሁ›› አቤቱ ማያተ ዮርዳኖስ አንተን አይተው ፈሩ ብሏል:: ይህንም አስመልክቶ ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ላይ ‹‹እምላዕሉ ወረደ ቃል አብ ወተሐውከ ማየ ዮርዳኖስ እምግርማ መለኮት›› ብሎ አብራርቶና ተርጉሞ ይነግረናል:: ትንቢቱ ይህ ነው::

ምሳሌ፡- ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ (ምንጩ) አንድ ነው፤ ዝቅ ብሎ በደሴት ይከፈላል። ዮር በእስራኤል በኩል ያለው ሲሆን ዳኖስ በአሕዛብ በኩል ያለው ነው። ዝቅ ብሎ እንደ ገና ይገናኛል። ጌታ የተጠመቀ በመገናኛው ነው። ሰውም ሁሉ ከላይ ነቁ መገኛው አንድ አዳም ነው፤ ከአዳም ተገኝቷል፡ ዝቅ ብሎ በደሴት እንደተከፈለ አሕዛብ በቍልፈታቸው እስራኤል በግዝረታቸው ተለያይተዋል። ዝቅ ብሎ በወደቡ እንዲገናኝ ሕዝብና አሕዛብም በጥምቀት አንድ ሆነዋልና።

ዳግመኛም ዮርዳኖስ በክረምት የማይሞላ በበጋ የማይጎድል ማእከላዊ ውኃ ነው፤ የጌታም ጥምቀቱ እኛን ከመጥቀም በላይ እሱን ከመጥቀም በታች ነውና። ማለትም ጌታ መጠመቁ ለእኛ ነው እንጅ ለእርሱ የሚጨመርለት ምንም ነገር የለምና።

ሌላው ኢዮብ ንእማን በዚህ በዮርዳኖስ ተጠምቀው ከደዌያቸው ተፈውሰዋል። ምእመናንም አምነው ተጠምቀው በጥምቀት ከፍዳ ከመርገም የመዳናቸው ምሳሌ ነው ‹‹ወበጥምቀተ ክርስትና ይከውን ሰብእ አግዐዜ ፍጹመ እምቅኔተ ሰይጣን ወእምአጋንንቲሁ ርኵሳን›› እንዲል።

ሌላው እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ እርስት ገብተዋል፤ ኤልያስም ዮርዳኖስን ተሻግሮ ብሔረ ሕያዋን ገብቷል (፪ ነገ፪ ፥፯) ምእመናንም አምነው ተጠምቀው ወደገነት ወደ መንግስተ ሰማያት የመግባታቸው ምሳሌ ነው።

አንድም አብርሃም ዮርዳኖስን ተሻግሮ በሄደ ጊዜ መልከጼዴቅ ኅብስተ አኮቴት ፅዋዐ በረከት ይዞ ተቀብሎታል (ዘፍ ፲፬፥፲፰) ይኸውም ምሳሌ ነው፤ አብርሃም የምእመናን፣ መልከጼዴቅ የቀሳውስት፣ ዮርዳኖስ የጥምቀት፣ ኅብስተ አኮቴት ፅዋዐ በረከት የሥጋው የደሙ ምሳሌ ነው። ትንቢቱ ምሳሌው ይህ እና ይህን የመሰለው ሁሉ ነው።

ምሥጢሩና መሰረታዊ አላማው፡- ግን 1ኛ የአዳምንና የሔዋንን የእዳ ደብዳቤ ለመደምሰስ ነው፤ ይኸውም ዲያብሎስ በአዳምና በሔዋን ሥቃይ አጽንቶ ስመ ግብርናታችሁን ጽፋችሁ ብትሰጡኝ አገዛዝ አቀልላቸኊለሁ አላቸው። እነርሱም እውነት መስሏቸው አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ ብለው ጽፈው ሰጡት። ያን በ፪ እብነሩካም ጽፎ አንዱን በሲኦል አንዱ በዮርዳኖስ ጥሎት ነበር። በዮርዳስ የጣለውን ሲጠመቅ፤ እንደ ሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶላቸዋል። በሲኦል የጣለውንም በዕለተ አርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ አጥፍቶላቸዋል።

አንድም ዮርዳኖስን ብርህት ፅድልት ማኅፀን ለማድረግ ነው። ስለዚህም የተጠመቅን የጥምቀት ልጆች ሁላችን ከዚህ ቅዱስ ማኅፀን የተገኘን የዚህ ቅዱስ ማኅፀን ፍሬዎች መሆናችን መርሳት የለብንም።

**ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ከእኔ አስቀድሞ የነበረ የእግሩን ጫማ ስንኳን ልፈታ የማይገባኝ ከእኔ ይልቅ የከበረ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነው። እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃችኋል በማለት መሰከረ።**

## ጌታ ጥምቀትን በውሃ ያደረገበት ምክንያት

1. የመጀመሪያው ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈፀም

ትንቢት ፦‹‹እነዝኀክሙ በማይ ንጹሕ ወትነጽሑ እምርኵስክሙ››ሕዝ ፴ ፮፥፳፭ ጥሩ ውኃን እረጫችኋለሁ ከርኵሰታችሁም ትነጻላችሁ ተብሎ ትንቢት ተነግሯል

ምሳሌ፡- ‹‹ ለታውፅእ ባህር ..›› ባለጊዜ በልባቸው የሚሳቡ በእግራቸው የሚሽከረከሩ በክንፋቸው የሚበሩ በደመነፍስ ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ፫ ፍጥረታት ተገኝተዋል፡፡ እሊህም በልባቸው የሚሳቡ አምነው ተጠምቀው በዚህ ዐለም የሚኖሩ የሰብአ አለም፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩ ከገድል ወደገድል፣ ከትሩፋት ወደትሩፋት የሚሄዱ የባሕታውያን፣ በክንፋቸው የሚበሩ ክንፈ ፀጋ፣ ተመስጦ ፀጋ ያላቸው የሰማዕታት፣ ባህር የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡

ምስጢሩ፡- ውኃ፤ በዙፋን ካለ ንጉሥ በአደባባይ እስካለ ፅኑስ (ደሀ) ለሁሉ ይገኛል፡፡ ጥምቀትም መሠራቱ አምኖ ለመጣ ሁሉ ነውና፡፡ ጌታ ጥምቀቱን በማር በወተት አድርጎት ቢሆን ባለፀጎች እንጂ ድሆች መጠመቅ አይችሉም ነበር፡፡ ስለ ዚህ ሁሉ በሚያገኘው በውኃ አደረገው፡፡ ዳግመኛም በውኃ የታጠበ ልብስ ኃይል ፅንዕ እየነሣ ይሄዳል፡፡ በጥምቀት የታደሰ ሰውነትም በጸጋ ላይ ጸጋ እየጨመረ ይሄዳልና፤ ዳግመኛም ውኃ የወሰደው እድፍ ፍለጋ የለውም ማለትም ከዚህ ደረሰ አይባልም፡፡ በጥምቀት የተሰረየ ሃጢአትም በፍዳ አያስይዝም፤ ዳግመኛም ሸክላ ሠሪ ከእቃዋ ነቅ ያገኘችበት እንደሆነ መልሳ ከስክሳ በውኃ ለውሳ ታድሰዋለች፡፡ ተሐድሶም በጥምቀት ነውና ስለዚህ በውኃ አደረገው፡፡ ‹‹ተቀደሰት ማይ በጥምቀቱ››

ጌታ በ፴ ዘመኑ የተጠመቀበትና እኛ በ፵በ፹ የተጠመቅንበት ምክንያት

## ጌታ በሰላሳ ዘመኑ የተጠመቀበት ምክንያት፡

1ኛ. በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት አንድ ሰው ለክህነት የሚሾመው በሠላሳ ዘመኑ ነው ዘኁ. 4፥3 ጌታም የቤተክርስቲያን ራስ የሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ስለሆነ በሠላሳ ዘመኑ ተጠመቀ፡፡

2ኛ. አዳም የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ በ40 ቀን ያገኘውን ልጅነት በአሊወ ሕግ አስወግዶ (አጥቶ) ነበርና ያን ለማስመለስ ዳግማይ አዳም ክርስቶስ ፈጻሜ ሕግ በሰላሳ ዘመኑ ተጠመቀ፡፡

እኛ ዛሬ በ40 በ80 ቀን የምንጠመቅበት ምክንያት አዳም በተፈጠረ በ40 ሄዋን በተፈጠረች በ80 ቀን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ አግኝተው በልጅነት ከብረው ብርሃን ለብሰው ብርሃን ተጎናጽፈው ገነት ገብተው ነበር (ኩፋ. 4፥9) ይህንን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

በኦሪቱም ይህን መሠረት አድርገው ወንድ በተወለደ በ40 ሴት በ80 መሥዋዕት ይዘው ቤተ መቅደስ ይገቡ ነበር፡፡ (ዘሌ. 12፥2-ፍጻሜው፤ ሉካ 2፥22)

ይኸውም በ30 ዘመን መጠመቁ አዳም የሠላሳ ዘመን ጎልማሳ ሁኖ መፈጠሩን ሲያስረዳን ነው፡፡

## ለሰው ልጆች የጥምቀት አስፈላጊነት

1. ለድኅነት - ለመዳን የግድ ጥምቀት ያስፈልጋል፡፡ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ማር 16፥16

2. ልጅነትን ለማግኘት- ስንጠመቅ ከሥላሴ ልጅነትን እናገኛለን፡፡ዮሐ 3፡5 ቲቶ 3፡5

3. ሥርየተ ሐጢአትን ለማግኘት በጥምቀት የሠራነው ኀጢአት ሁሉ ይደመሰሳል፡፡ የሐዋ 9

4. ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን ለመዋሐድ፡፡ ገላ 3፡ 27

5. ክርስቶስን ለመምሰል- ወደ ውሃው መግባታችን

የሞት፣ ብቅ ጥልቅ ብለን ብርሃን ለብሰን መውጣታችን የትንሣኤ ምሳሌ ነው (ቆላ 2፡12)

የእኛ ጥምቀት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች እንመለከታለን:: ይኸውም የልጅነት፣ የንስሓ፣ የበረከትና የፈውስ ናቸው:: ከዚህም መካከል አንዱ ለመዳን የግድ አስፈላጊ ነው:: ፪ቱ ግን እንደአስፈላጊነታቸው ብቻ ይፈጸማሉ:: እሊህንም በአጭሩ በዝርዝር መመልከት ይገባል

**እኛ ዛሬ በ40 በ80 ቀን የምንጠመቅበት ምክንያት አዳም በተፈጠረ በ40 ሄዋን በተፈጠረች በ80 ቀን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ አግኝተው በልጅነት ከብረው ብርሃን ለብሰው ብርሃን ተጎናጽፈው ገነት ገብተው ነበር (ኩፋ. 4፤9) ይህንን መሰረት በማድረግ ነው።**

## ሀ/ የልጅነት ጥምቀት (ማየገቦ)

ይህንን ጥምቀት በማየ ገቦ ተጠምቀን ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማሕፀነ ዮርዳኖስ ተወልደን ሥላሴ በኛ የሚያድሩበት እኛ ከሥላሴ ጋር የምንወሓድበት የክርስቶስ አካል ቤተሰብ የምንሆንበት አማናዊና መሰረታዊ የመዳን ጥምቀት ነው:: ለመዳን ይህ የልጅነት ጥምቀት የግድ አስፈላጊ ነው:: ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያናችን ከሚፈጸሙት 7 ምስጢራት መካከል ለመዳን የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ለመወለድ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ምስጢረ ጥምቀት፣ ምስጢረ ሜሮን፣ ምስጢረ ቁርባን እሊህ 3ቱ የግድ መፈጸም አለባቸው:: አንድ ሰው እሊህን 3ቱን ምስጢራት ካልፈጸመ ክርስቲያን ሊሆን የእግዚአብሔርም ልጅ ሆኖ ሊወለድ ወደእግዚአብሔርም መንግሥት ሊገባ አይችልም:: ይኸንም ሲያስረዳ ጌታችን በወንጌል ምስጢረ ጥምቀትን ባስተማረበት አንቀጽ ‹‹ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን›› ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል (ማር 16፡16) ዳግመኛም (ዮሐ 3፡ 5) ‹‹ዘኢተወልደ ዳግመ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ›› ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም:: እንዲሁ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ‹‹ክርስቶስ ተወልደ ክርስቶስ ተጠምቀ ወለደነ ዳግመ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ›› ክርስቶስ ተወለደ ክርስቶስ ተጠመቀ እኛንም ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ወለደን::

### ይህንም የልጅነት ጥምቀት በ3 መንገድ እናገኘዋልን።

1. አሁን እንደተናገርነው በቀጥታ ሥርዓቱ ተፈጽሞ (ተከናውኖ) በውኃ በመጠመቅ የሚፈጸም የውኃ ጥምቀት (ማየገቦ)

2. ደመ ሰማዕት (የደም ጥምቀት) ወይም የመከራ ጥምቀት ይባላል:: ይህም የሚፈጸመው ቀድሞ

ኢአማኒያን የነበሩ አህዛብ ቅዱሳት ሰማዕታት ሲጋደሉና መከራ ሲቀበሉ እንዲሁም ተአምራት ሲያደርጉ አይተው በቅዱሳኑ አምላክ በአምላክ እገሌ አምነናል እያሉ ስለ ክርስቶስ እየመሰከሩ ገና ለጥምቀት ሳይበቁ በአላውያን አደባባይ የሰማዕትነት ጽዋ እየቀመሱ ያረፉ አባቶቻችንና እናቶቻችን መከራቸው ስቃያቸው ጥምቀት ይሆንላቸዋል:: ይህንም ጌታ ለመሰቀል ወደ ኢየሩሳልም እወጣለሁ ሲል ዮሐንስ እና ያዕቆብ ለሹመት መስሎአቸው ነበር:: ጌታም የምትለምኑትን አታውቁም ብሎ እኔ የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን ብሎአቸዋል:: ይህም እኔ የምቀበለውን መከራ ሲል ነው:: ማቴ 20:22

3. አንብአ ንስሓ፡- ይህም ኢአማንያን አምነው ንስሓ ገብተው ገና ለመጠመቅ በዝግጅት (በንስሓ) ላይ ሳሉ ለጥምቀት ሳይበቁ በድንገተኛ አደጋ ቢያርፉ ዕንባቸው ንስሓቸው ጥምቀት ይሆንላቸዋል:: ይህም ሦስት ያልነው የአፈጻጸም ስልቱን ነው እንጂ ጥምቀት አንዲት ናት:: አባቱም ያው አንድ ነው እንጂ ልዩ አይደለም:: ይህ እስካሁን የተናገርነው አማንያን በውድም ሆነ በፈቃድ አምነው የሚጠመቁት ጥምቀት ሲሆን፤ ነገር ግን ዛሬ ይህን የልጅነት ጥምቀት ያልተጠመቁ ኢአማንያን ኋላ በፍርድ ቀን በገሃነም የሚጠመቁት ለመንግሥተ ሰማያት የማያበቃ ባሕረ እሳት የሚባል፤ 4ኛ የመከራ፣ የእሳት ጥምቀት አለ ማቴ. (3:11) እሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት ያጠምቃቸዋል:: ይህም ማለት እሽ ብትሉ በመንፈስ ቅዱስ እንቢ ብትሉ በእሳት ያጠምቃችኋል::

## ለ/ የንስሓ ጥምቀት (ቄደር)

ይህ የንስሓ ጥምቀት የሚከናወነው

1. በእምነቱ ውስጥ የነበሩ አማያን ከእምነቱ ወጥተው ወደ ሌላ እምነት ሂደው ቆይተው በሚመለሱበት ጊዜ የንስሓ ጥምቀት (ቄደር) ይጠመቃሉ::

## ሐ/ የፈውስ ጥምቀት

የተለያየ በሽታ ያለባቸው ሰዎች በቅዱሳን ስም በፈለቁና በከበሩ ፀበሎች ለፈውስ ለበረከት የሚጠመቁት ጥምቀት ነው:: (ዮሐ 5)

ማጠቃለያ፡- እንደ ዮሐንስ አስተምሮ ተጠማቂዎች ሊያሙዋሏት የሚገባ ነገር (ሉቃ 3:3-18) ሊጠመቁ ለመጡት ሕዝቦች እንዲህ ይላቸው ነበር::

1. ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አድርጉ (ጾም፤ ጸሎት፤ ስግደት
2. ሁለት ልብስ ያለው ለሌላው ያካፍል፤ ምግብም ያለው እንዲሁ (ምጽዋት)
3. ለቀራጮች ፤ ከታዘዛችሁት አብልጣችሁ አትውሰዱ
4. በደመወዛችሁ ኑሩ፤ የሰው ገንዘብ አትውሰዱ (መማለጃ አለመቀበልን)
5. ጎድጎዳው ይሙላ፤ ጎባጣው ይቅና (የአመለካከት ለውጥ)
6. ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ (የጥምቀትን አዳኝነት)

እንዲህ በማለት የሚጠመቁ ክርስቲያኖች ሁሉ በምግባር በሃይማኖት ፍጹም እንዲሆኑ ይመክር ያስተምር ነበር:: እኛም በዚህ በዮሐንስ ትምህርት ጸንተን የበረከተ ጥምቀቱ ተሳታፊዎች እንድንሆንና መንግሥቱን እንድንወርስ ልዑል እግዚአብሔር ይፍቀድልን፤ አሜን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*